የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፳፫
አዲስ አበባ–የካቲት ፲፯ ቀን ፲፱፻፺

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

4th Year No. 23
ADDIS ABABA - 24th February, 1998

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፻/፲፱፻፺ ዓ·ም·
የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ ፵፫(፪) ማሻሻያን ማጽደቂያ አዋጅ ........................................ ገጽ ፮፻፺፫

## CONTENTS

Proclamation No. 100/1998
Amendment to Article 43 (2) of the Convention on the Rights of the Child Ratification Proclamation ........................................ Page 693

### አዋጅ ቁጥር ፻/፲፱፻፺

### የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ ፵፫(፪)ን ማሻሻያ ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ኢትዮጵያ ቀደም ሲል ባጸደቀችው የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ ፵፫(፪) ላይ ፣ በኮንቬንሽኑ አባል ሀገሮች ጉባዔ እ·ኤ·አ· ዲሴምበር ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፭ ፣ የተደረገውን ማሻሻያ ከደገፉት አንዷ በመሆኗ ፤

በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ እ·ኤ·አ· ዲሴምበር ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፭ ተቀባይነት የተሰጠው ማሻሻያ የሚጸናው፣ ከኮንቬንሽኑ አባል ሀገሮች ሁለት ሦስተኛው በኮንቬንሽኑ አንቀጽ ፶(፪) መሠረት ሲያጸድቁት ጭምር ስለሆነ፤

ይህንኑ ማሻሻያ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የካቲት ፲፯ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም· ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ ፤

በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

### PROCLAMATION No. 100/1998

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE AMENDMENT TO ARTICLE 43 (2) OF THE CONVENTION ON THE RIGHTS OF THE CHILD

WHEREAS, at the conference of States Parties held on 12 December 1995, Ethiopia adopted the amendment to Article 43 paragraph (2) of the Convention on the Rights of the Child, which it had earlier ratified;

WHEREAS, the Amendment approved by the General Assembly of the United Nations on 21 December 1995, enters into force subject to acceptance by a two-thirds majority of States Parties, pursuant to Article 50 paragraph(2) of the Convention;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said amendment at its session held on the 24th day of February, 1998;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ማሻሻያን ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፻/፲፱፻፺" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· <u>ማሻሻያው ስለመጽደቁ</u>

የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ እ·ኤ·አ· ዲሴምበር ፳፩ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ·ም· የተቀበለው በሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ ፵፫(፪) ላይ የተደረገ ማሻሻያ ጸድቋል ።

፫· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከየካቲት ፲፯ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም· ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፲፯ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Amendment to the Convention on the Rights of the Child Ratification Proclamation No. 100/1998."

2. *Ratification of the Amendment*

The Amendment to Article 43 (2) of the Convention on the Rights of the Child, approved by the General Assembly of the United Nations on 21st December 1995, is ratified.

3. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 24th day of February, 1998.

Done at Addis Ababa, this 24th day of February, 1998.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE